**በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣**

**ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ**




# ከሴፕቴምበር 21-30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከኦክቶበር 1-10፣11-20/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ31 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.2-62.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች አቦሞሪንጋ 62.4፣ አይራ 55.2፣ አታንጎ 60፣ በደሌ 48፣ ቦሬ 40.2፣ እርምጭ 48.8፣ ፉኝዶ 52.1፣ ጊኒር 50.5፣ ቀብሪዳር 55.4፣ ማንኩሽ 48.4፣ ነቀምት 46.7፣ ሸርቆሌ 42.4ይገኙበታል ፡፡




ምስል1:ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ከአማራ ክልል የምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና መዠንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል ቆራሂ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ ላይ ከ31-180 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቦርና፣ ምስራቅ ቦርና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ከአማራ ክልል የምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና መዠንግ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች ከሶማሌ ክልል ቆራሂ፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ በአብዛኛ መደበኛ እና ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብ ኢጋማሽ፣ በሰሜን ምዕራብ፤ በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም በወቅቱ መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንድሁም ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ በነበሩትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤና ላይኛው አባይ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ፍሰት ነበረቻው፡፡ የህም ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ግብዓት ጥሩ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5) ።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ በመሆኑም የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ ለደቡብ አጋማሽ አከባቢዎች የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት የዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር የመጀመሪያዋቹ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ እና ላይ ከቀላል እስከ መከከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1-10/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ እና ጅማ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ እና ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የአዊ፣ ምዕራብ ጎጃም እና ባህርዳር ዙሪያ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ እና መዥንግ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል እና ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ ደቡባዊ ስፍራዎች፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ እና ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ደራሼ እና ኮንሶ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |

Ethiopian Meteorology

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.4 እ.አ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ከኦክቶበር የመጀመርያዎቹ አስር ቀናት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመኸር አምራች ዞኖች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ረርጌ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም ፣ ባህርዳር ዙሪያ ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አኝዋክ ፣ መዥንግ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ | ➢ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በሰብሎች ላይ መተኛት<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘሩ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ የድጋሚ አረምን ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበርቤላ |

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | | |
|---|---|---|---|
| ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ደራሼ፣ ኮንሶ፣<br>ሶማሌ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች | ➢ የበጋ ተጠቃሚ ደጋማ ስፍራዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | ➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • ባሮ አኮቦ፣ በላይኛውና መካከለኛ አዋሽ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት በላይኛዉ የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ በመጠኑ መሻሻል | •<br>• የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • በላይኛዉ ዋቤ ሸበሌና ታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከላከል |
| **ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በአብዛኛው አፋር ደናከል፣ መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ አዋሽ፣ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | • የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ<br>• ከፍተኛ ትነት | • የውኃ እጥረት በሚገጥማችው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር<br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |